# “የመለስ ራዕይ” የሁለት ዓመታት ጉዞ ሂሳዊ ግምገማ

ዮናስ 08-29-14

ለጓድ መለስ ዜናዊ ከድህነት በላይ ክፉ ጠላት የሌለ መሆኑ እሙን ነው፡፡ አቶ መለስ በድህነት የተቆራመዱና ጠኔ እየገፋቸው የሚኖሩ፣ የሚለብሱት አጥተው በእርዛት የሚቸገሩና በመጠለያ እጦት ምክንያት ባረጁ ጎጆዎች ተጨናንቀው የሚያድሩ ዜጎች ሃገር ይዘን እንቅልፍ ተኝተን ልናድር አይገባም፡፡ ስለዚህም ጠላታችን የሆነውን ድህነትን በማጥፋት ዜጎቻችንን ሰብአዊ ክብር ማላበስ፣ ሃገራችንንም ከተስፈኞች ጎራ ማውጣት አለብን የሚል ፅኑ አቋም የነበረው ሲሆን ከዚህ አኳያ የሃገራችን እድገት ጎልቶ እንዲታይ ያደረጉት የከተማና የገጠር ልማት ፖሊሲዎችና የአፈፃፀም ስልቶች የመለስን የልማት አርበኝነት እና ጀግንነት በትክክል የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ከድህነት በላይ ጠላት ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ላሣር ነው፡፡ ጠባችን ከድህነት እና ውጊያችን እና የጦርነት ውሎአችንም በማሳ ላይ እንጂ በጦር አውድማ ላይ አይደለም፡፡ በዚህ ሰዓት የእኛ ጀግኖች በማሣ ላይ የጀገኑት ናቸው፡፡ የሚለው የመለስ የማይናወጥ አቋም ሲሆን በውስን ውጤት ሳይረካ ታላላቁን በመመኘት ደፍሮ ያደፋፈረን ታግሎ ያታገለን ጀግና መሪ ነበር፡፡

የመለስን አርበኝትና ጀግንነት የሚያመላክቱ ሌሎች ነጥቦችም አሉ፡፡ መለስ ብዝሃነትን ማክበር የአገሪቱ ህልውና መሠረት መሆኑን አጽንኦት ሠጥቶ ሳይታክት አሥተምሯል፡፡ በገዛ አገራቸው ተዘግተው የኖሩ የተናቁና ማንነታቸው፣ እኩልነታቸው የተገፉ ወገኖች እኩል ሰው መሆናቸው ታውቆ በአገሪቱ ወሣኝ ተግባራት እኩል ተሣታፊና የውጤቱም እኩል ተጠቃሚ፣ የአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ነፃና ህያው አካል እንዲሆኑ በሠፊው ተንቀሳቅሶ አንቀሳቅሷል፡፡ ከዚህ በላይ ምን ሃዋርያዊ ተልዕኮ እና አርበኝነት ይኖር ይሆን??

መለስ የአገራችን ህዝቦች ከአንድ ውሱን አካባቢ በወጡ ገዢዎች ጭቆና ሥር ሲማቀቁ እንደነበሩ፣ ያ አገዛዝ ለዛም አካባቢ ህዝብ ያልጠቀመ እንዲያውም እንደሌሎች ህዝቦች ሁሉ የግፉ ተሸካሚ እንደነበረ በማሣየት የአገራችንን ህዝቦች ሁሉ ትግል በማስተባበር የሠራ፣ ትግሉን ከመላ የአገሪቱ ህዝቦች ጋር የአገሪቱን ህዝቦችም ከትግሉ ጋር ያስተዋወቀና

የስተማረ ብልህና ታላቅ መሪ ነው፡፡ የመለስ የአስተሳሰብና የድርጊት መርሆ ማእከላዊ ነጥብ ድሪቶ መጣፍ ሳይሆን አዲስ አስተሳሰብ ማላበስ፣ ድህነትን መርታትና በድህነት ለዘመናት ተጠምዶ የማቀቀውን ህዝብ የብልጽግና ምንጭ እንዲሆን ማብቃት ነው፡፡ ቀዳማዊ ዓላማው የሚያስታግሠውን ሳይሆን፣ የሚፈውሠውን መሻት ነው፡፡ የደከመው የወደቀው ለመትረፍ ከመፍጨርጨር አልፎ ኑሮውን አሸንፎ ምኞቱ ለወገኑና ለአገሩ መድረስ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

መለስ ለሁሉም ነው፤ መለስ የሁሉም ነው !! ለምን? ቢሉ መለስ ለአገራችን ህዝቦች ልማት፣ እኩልነት፣ ለሠላም እና  ዴሞክራሲ ባደረገው ተጋድሎ  የሁሉም ብሄረሰቦች አባል ለመሆን የበቃና የሁሉም ማህበረሠቦች ማለትም የአርሦ አደሩ፣ የአርብቶ አደሩ፣ የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የከተማ ነዋሪው፣ የባለሃብቱ ወዘተ አካል መሆን የቻለ መሆኑ ነው፡፡

መለስ ለዓላማው ሲል እስከ እለተ ሞቱ፣ ከአንድ ትውልድ በላይ ለሆነ ዘመን በታታሪነት ሲታገል የኖረ፣ ስለግል ጥቅሙና ምቾቱ የማያስብ፣ የግል ዝናና ክብር የማያማልለው ታጋይና ህዝባዊ መሪ ነው፡፡ ዘወትር ከአንደበቱ ከድህነት በላይ ጠላት የለንም የሚለው አባባል አይጠፋም። ትኩረቱ ሁሉ ከወጣትነቱ ጀምሮ በልቡ ውስጥ የሠረፀውን የህዝቦችን ሰቆቃ የማስቀረት ራዕይ ማሳካት ላይ ብቻ ነበር፡፡ የዚህን ጀግና መሪ ራዕይ ማሳካትም የትውልዱ ተልዕኮ ነው፡፡

እስከዛሬ እንደተመለከትነው፣ የአገራችን የከሰሩ ፖለቲከኞች ሞቷል፤ ሞቷል ሲሉ መለስ ላይ ያላቸውን በዘረኝነት ላይ የተመሰረተ የግልና ጥላቻ ያራግፋሉ እንጂ በርግጥም ፍሬ ነገር ያለው ወሬ ለማውራት አልታደሉም፡፡ ስሜታዊነት ደግሞ  ለቁምነገር በር አይከፍትም፤ ጥርቅም አድርጎ ይዘጋል እንጂ፡፡ እነዚህ ወገኖች ሲሉት እንደነበረው *መለስ ህግ አይደለም፣ ህግም መለስ አልነበረም፡፡* ባንፃሩ መለስ ዴሞክራሲያዊ እሴቶችን የህይወት መመሪያው ያደረገ፣ በህግ የበላይነት የሚያምን፣ ራሡን የመንግስት ባለስልጣናትንና ድርጅቱን ከህግ በታች አድርጎ የማይመለከት በሣል መሪ እንጂ፡፡ መለስ በአገራችን የህግ የበላይነት እንዲሠፍን፤ የፍትህ አካላት የህግ አስከባሪ ተቋማት እና ሌሎች የዴሞክራሲ ተቋማት እንዲጠናከሩ እና በዴሞክራሲያዊ እሴቶች ላይ እንዲመሠረቱ ወሣኝ አመራር የሰጠ ጀግና መሪ ነው፡፡ ጀግንነቱ ደግሞ በእንደዚህ አይነቱ ትርጓሜ ብቻ የሚገለጽ አይደለም፡፡  ደርግን የሚያህል፣ የአፍሪካ ግዙፍ ሠራዊት መለስና ጓደኞቹ ናቸው የጣሉት፡፡  ድሉ ደግሞ ጠሩን በበላይነት ሢመሩ፣ ታግለው ሲያታግሉ

ከነበሩ ግለሰቦች የሚመነጭ ነው፡፡ ከእነዚህ ታጋይና አታጋዮች መሃከልም መለስ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ነው፡፡ ስለሆነም መለስ የልማት አርበኛ፣ የሰላም ሃዋርያ እና ጀግና ብቻ ሳይሆን የጦር ግንባር አርበኛና ለክቡር ዓላማው ሲል ጥይት የበማማው ጀግና ነው፡፡ መለስ ህግ ስላልሆነ ህግም መለስ ስላልሆነ ለዘመናት ጨቋኝ ሆነው የኢትዮጵያውያንን ደም ሲያፈሱ የነበሩ የደርግ ባለሥልጣናትን በህግና በህግ ብቻ እንዲዳኙ እና የበቀል እርምጃ እንዳይኖር ቁርጠኛ አቋም በመውሠድ ባለስልጣናቱ በህግ ውሣኔ እንዲያገኙ በጽኑ እምነት አመራር የሰጠ ታላቅ መሪ መሆኑን ነው ሁላችንም የምናውቀው እና በእርግጠኝነት መናገር የምንችለው፡፡

የከሰሩቱ ረክሠው ለማራከስ የፈለጉት መለስ እንኳንስ ለእኛና ለጎረቤቶቻችን ስለ አፍሪካ ሠፊና ጥልቅ እውቀት ያለው በመሆኑ የአካባቢው መሪዎችና ታዋቂ ሊቃውንት ዘወትር የእርሡን አስተያየትና ምክር ይጠይቃሉ፡፡ በጠላትነት የሚፈላለጉ ሃገራት መለስ በሚያቀርባቸው መሰረታዊ የሠላም ሃሳቦች ላይ ያለምንም ማወላዳት ይስማማሉ፤ ለዚህም የሱዳንን ጉዳይ ማስታወስ በቂ ነው፡፡

በዚህ ብቻ የማያበቃው የመለስ ገድልና ታምራት በዓለምና በአፍሪካም ተገልጧል፡፡ “የአፍሪካ ድንቅ ልጅ” የሚል ስያሜን ያተረፉሉትን የተለያዩ ተግባራት አከናውኗል፡፡ የአፍሪካ ምርቶች ዋጋ እንዲሻሻል፣ ወደ አፍሪካ የሚፈሠው ኢንቨስትመንት፣ ብድርና እርዳታ እንዲጨምር፣ አፍሪካውያን በአየር ንብረት መዛባት ለሚደርስባቸው ጉዳት ማካካሻ እንዲያገኙ እንዲሁም የዓለም ንግድ ሥርዓት ለአፍሪካ ዕድገት የሚያመች እንዲሆን ለማድረግ በተገኙት መድረኮች ሁሉ ሳይታክት ታግሏል፡፡

የአፍሪካውያን ጥቅም የሚረጋገጠው በተናጥል በሚደረግ መፍጨርጨር ሳይሆን በመሠረታዊ የጋራ ጥቅም ጉዳይ ላይ የጋራ አቋም በመያዝ፣ በዓለም አቀፍ መድረኮች በአንድ ድምፅ በመሠለፍ መሆኑን መለስ ከልቡ አምኖ ታግሎ አፍሪካውያን መሪዎችን በማታገል በዓለም አቀፍ ደረጃ ባለራዕይ አፍሪካዊ መሪ፣ የአፍሪካ ልሣን፣ የሚሉ ማዕረግ ስሞችን ተጎናጽፏል፤ “Mother Africa” በሚላት አፍሪካ ባሉ አፍሪካውያንም ከፍተኛ አድናቆትን እና አክብሮትን አትርፏል፡፡

መለስ የላቀ ህዝባዊ ፍቅር ያለው መሪ ነበር፤ ይህም ጥልቅ ህዝባዊ ፍቅር መለስን እያንዳንዱን ጉዳይ ከህዝቦች መሰረታዊ ጥቅም አኳያ እንዲመዝን አድርጎታል፡፡ የህዝቦች

ሠቆቃ የሚያንገፈግፈው፣ ለህዝቦች ጥቅምና ጀግንነት፣ ለህዝቦች ሠላም ወዘተ  ሌት ከቀን የሚጨነቅ፣ ይህንን ፍቅሩን የሁሉም ተግባራቱ አንቀሣቃሽ ሞተር አድርጎ የሚጠቀም . . . መሆኑ መለስን ጀግና ብቻ ሳይሆን የጀግና ጀግና አድርጎታል፤ የህዝቦቹን ፍላጎት የሚያነፈንፍ፣ ለህዝብ የቀረበ ልብ ያለው በሳልና አስተዋይ መሪ፡፡ ሃዋርያም ተብሎ ተጠርቶበታል፡፡ “ለእኔ ሃገር ማለት ህዝብ ማለት ነው፡፡ የአገር ፍቅርም ማለት ከህዝብ ፍቅር ውጪ ትርጉም የለውም” አስተሳሰቡ ሁላችንንም ያስደመመ፣ እሱንም ያደነቅንበት፣ ምርጥና ዘላቂ ሃሳብ መሆኑን ዓለም የመሠከረለት፣ አንዱ የመለስ መለያና ፖለቲካዊ ባህሪይ ነው፡፡ ህዝብ በተክክለኛ ድርጅት ከተመራ ታሪክ ሊሠራ የሚችል መሆኑን አምኖ ወደ ጥቅሙ የሚያመራውን አቅጣጫ ለማስያዝ መለስ ሁልጊዜ ሣይታክት የሠራና ያለውን ቁርጠኝነት በተግባር ያረጋገጠና በመስዋእትነት ያሳየ መሪ ነው፡፡

በመሆኑም መለስ በአንድ ጊዜ የፖለቲካ ሳይንቲስት፣ የኢኮኖሚ ሊቅ፣ የማህበራዊ ሳይንስ ተንታኝ፣ የህግ ምሁርና የወታደራዊ ሣይንስ ጥበብ ቁንጮ ነበር፡፡ በዚህም ጀግና ቢባል፣ ሃዋርያ ቢባል፣ አርበኛም ቢሠኝ ቢያንስበት እንጂ የሚበዛበት አይሆንም፡፡ ስለማያንስበትም ነው መላ ህይወቱን ላመነበትና ለቆመለት ዓላማ መስዋእት የሆነውን ታላቅ መሪ ራዕይ ለማስቀጠል ሁሉም የሡን ራዕይ፣ የሡን ዓላማና ግቦች አንግቦ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው፡፡ ያም ሆኖ ግን ሁላችንም በየተሰማራንበት ዘርፍ የመለስን ራዕይ ለማሳካት፣ የታላቁ መሪን ሃዘን ልናወራርድም ሆነ ቁጭታችንን በመወጣት ለዚህች ሀገር የነበራቸውን ተስፋና ራእይ እንዲሁም ጅምራቸውን በመጨረስ የሃገራችን መጪውን ብሩህ ቀን ለማሳካት ቃል ከገባን 2 ዓመት የሆነን መሆኑ የተዘነጋ አይመስለኝም፡፡ ነፍሳቸውን በአፀደ ገነት እንዲያኖርልን በዚህ አጋጣሚ ለታላቁ መሪ በየእምነታችን በፀሎት እያሰብን ልናሳካ የገባነውን ቃል ወደኋላ መለስ ብለን ማየት ያለብን ጊዜ ላይ የምንገኝ መሆኑ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ አፅንኦት እንዲሰጠው ይሻል፡፡ ለምን ቢሉ ከዚህ በታች የተመለከቱትን እና የአቶ መለስን ግብና ባለራዕይነት የሚያረጋግጡ ማሳያዎች ተመልክተን የገባነውን ቃል ስንመዝነው ቃላችንን ያጠፍን ስለሚመሰልብን ነው፡፡ ከሁሉ የሚልቀው ደግሞ በእርግጥ አቶ መለስ ከሁሉ በላይ በሆነውና በአረንጓዴ ልማት ዘርፍ ባላቸው ራዕይ ቢታወቁም ከዚህና አለማቀፋዊ ገፅታ ካለው ራዕይ ባሻገርም ለሃገራችን የልማትና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ወሳኝ በሆኑቱ ከላይ የተመለከቱ የባለራዕዩ መሪ ውጥኖች አኳያ አንድ በአንድ እኛነታችንን መፈተሽ ይገባናልና ነው፡፡ የታላቁን መሪ ሁለተኛ አመት በመዘከር

በሃገር አቀፍ ደረጃ በአረንጓዴ ልማት ዘርፍ ሰፊ እንቅስቃሴ እየተደረገ ቢሆንም በዚህም ዘርፍ ያለፉት ሁለት አመታት ሲፈተሹ አፈፃፀሙ በጎ ቢሆንም እንደሳቸው ራዕይ አመርቂ ነው አያስብልም፡፡ በታላቁ መሪ ስም በተቋቋሙ ፓርኮች ላይ ከተተከሉት ችግኞች በአማካይ የፀደቁት ከ70 በመቶ አለመብለጣቸው ሰሞንኛ ዜና ነው፡፡ መንከባከብን ባላካተተ፣ መትከልን ብቻ ግብ ባደረገ እንቅስቃሴ ደግሞ የተፈለገውን ለውጥና ራዕያቸውን ማሳካት አይቻልም፡፡

አንዳንድ መ/ቤቶች በእርሳቸው ስም በከለለበት ፓርክ ላይ ለተከሏቸው ችግኞች ከደሞዛቸው ቆርጠው ተንከባካቢ ባለሙያ የቀጠሩበትን እና ያለ ብዙ ወጪ ራዕያቸውን ለማሳካት ከጫፍ ላይ የመገኘታቸውን ተሞክሮ ሌላውም ቢወስደው መልካም ነው፡ ለመጠቆም ያህል እንጂ ያለብዙ ወጪና ድካም ሌላ መላ የዘየዱ ሊኖሩ እንደሚችሉ ጥርጣሬ አይኖርም፡፡ ዋናው ጉዳዬ ግን መለስን ስናስብ ሁለት አመት ሆኖናልና "እገሌ የተባለ መ/ቤት ሰራተኞች፣ በእገሌ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ባለሃብቶች፣ ነጋዴዎች ወጣቶች ወዘተ የመለስን ራዕይ በዚህን ያህል ፐርሰንት ማሳካታቸውን አረጋገጡ፤ ማረጋገጣቸውንም ተገልጋዩ ህብረተሰብና ተጠቃሚው ህዝብ እንዲህ ሲል እየመሰከረ ነው፡፡" የሚል ዜና መስማት የሚገባን ሰዓት ላይ ሆነን ዛሬም የእገሌ መ/ቤት ሰራተኞች፣ ባለሃብቶች ወዘተ የመለስን 2ኛ ሙት አመት ምክንያት በማድረግ ራዕያቸውን እናስቀጥላለን አሉ የሚል ዜና እንደ ዛሬው ሁለት አመት ማድመጣችንና ማየታችን ነው ስጋቴ፡፡ ዛሬ ላይ ስንናፍቅ የነበረው "እናስቀጥላለን" ሲሉ የተናገሩትን መስማትና ማየት ሳይሆን ማስቀጠላቸውን የሚመሰክር ህዝብ ማየትና መስማት ነበር፡፡ ይህ ያልሆነው ደግሞ ዘጋቢዎቻችን፣ ዜና መሆን ያለበት የትኛው እንደሆነ ጠፍቷቸው አይመስለኝም፤ ይልቁንም የሆነው እንዲህ ስለሆነ ነው፡፡

ግብርና መር በሆነው የኢንዱስትሪ ሃገራዊ ፖሊሲ ባለ ሁለት አሃዝ አገራዊ እድገት መመዝገቡ እሙን ነው፡፡ ይህ ደግሞ የመለስ ራዕይና ራዕዩን ለማስቀጠል ቃል የገቡት አርሶ አደሮችና የግብርና ባለሙያዎቻችን ቃላቸውን በመጠበቃቸው የተገኘ ውጤት ነው፡፡ ታላቁ መሪ በዚህና በትራንስፎርሜሽኑ የዕቅድ ዘመን ይሳካ ዘንድ የወጠኑት ራዕይ ደግሞ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ በኢንዱስትሪው የሚተካበትን ዕድሜ ማሳጠር ነው፡፡ ለማሳጠር የሚያስችሉ ግብአቶችንና ስትራቴጂዎችንም ቀርፀውልን አልፈዋል፡፡ በእነዚህ ግብአቶችና ስትራቴጂዎች ታግዘው ራዕያቸውን እውን ያደርጉ ዘንድ የሚጠበቅባቸው (በይበልጥ) ደግሞ

ልማታዊ ባሃብቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ባለሀብቶችም የታላቁን መሪ ራዕይ ለማስቀጠል ቃል መግባታቸውን እናስታውሳለን፡፡ ያም ሆኖ ግን የሚበዙቱ ባለሀብቶቻችን አሁንም የሚገኙት በንግድና አገልግሎት ዘርፍ ላይ ተጣብቀው ነው፡፡ እሴት ባልተጨመረበት የወጪ ንግድ ዘርፍ መሰማራታቸው ደግሞ የታላቁ መሪ ራዕይን ለማስቀጠል ከገቡት ቃል ጋር የሚጣረስ ነው፡፡

ታላቁ መሪ በእቅዱ ዘመን የማምረቻ ኢንዱስትሪውን ዘርፍ 17 በመቶ ለማሳደግ ወጥነው ሲያበቁ የሚያሰራ ፖሊሲና ድጋፍም ነድፈውና አስተማማኝ የሰው ሃይል የሚፈራበትን የትምህርት ስርዓት አበጅተውልን ነበር፡፡ ያም ሆኖ ግን ራዕያቸውን ለማስቀጠል ቃል የገቡት ባለሃብቶቻችን ተሳትፎ አሁንም ገና 5 በመቶ ላይ ነው፡፡ ሰሊጥና ቡናችንን እየላክን ያለነው በብላሽ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ ሰሊጥን ብቻ እንኳን አበጥረን ብንልከው አሁን በሚገኘው የውጭ ምንዛሬ ላይ የ30 በመቶ የዋጋ ጭማሪ እንደሚኖረውም ይታወቃል፡፡ ያም ሆኖ ግን የታላቁን መሪ ራዕይ የበሉ ባለሀብቶቻችን እስከአሁንም አየር በአየር ከሆነና ለበርካቶች የሥራ እድልን ፈጥረው የውጭ ምንዛሬያችንን በሚያደልቡ ዘርፎች ላይ ሊሰማሩ የፈቀዱ አይመስልም፡፡ አስተማማኝ ግብአትና የሠው ሃይል መኖሩ ግልፅ በሆነበትና በቂ የሆነ የግብር የእፎይታ ጊዜ መንግስት እንደሚሰጥ ግልፅ በሆነበት አግባብ የኮንስትራክሽን እቃዎችን ከውጭ እያመጣን ያለው በበርካታ የውጭ ምንዛሪ ነው፡፡ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶቻችንን በሴራሚክ ዘርፍ ብቻ ስናያቸው ተሳትፏቸው 5 በመቶ ብቻ እንደሆነም ሰነዶች ያረጋግጣሉ፡፡ የወጭ ንግዳችን በየዐመቱ ሙሉ በሙሉ እቅዱ ተሳክቶ የማያውቀውም የታላቁን መሪ ራዕይ እናስቀጥላለን ብለው ቃላቸውን በዘነጉ ባለሀብቶቻችን ነው፡፡

የመለስ ራዕይ ከላይ በተመለከቱት ጥቂት ጉዳዮች እንኳ ሲታይ እንዲህ በቀላሉ የሚለካ አይደለም፡፡ የእርሳቸው ራዕይ ኢትዮጵያን በአፍሪካ ጠንካራ የኢኮኖሚ ባለቤትነትን እንዳጎናፀፋት አለም አቀፍ የብዙሃን መገናኛዎች በተደጋጋሚ የዘገቡት ጉዳይ ነው፡፡ ኤሲያን በዚነስ ኮርፖሬት የተባለ አለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን ሰሞኑን ባሰራጨው ዘገባ ኢትዮጵያን የአህጉረ አፍሪካ የተስፋዋ ምድር ሲል ገልጿታል፡፡ የዐለም ባንክ ሪፖርት በበኩሉ *ከ16 ዓመት በፊት የነበረው የኢትዮጵያ አገራዊ ምርት 15 ቢሊዮን ዶላር የነበረ ሲሆን ዛሬ ላይ በታላቁ መሪ ራዕይ በ4 እጥፍ በልጦ 42.8 ቢሊዮን ዶላር መድረሱን* አረጋግጧል፡፡ ይህም አገሪቱ ከአፍሪካ 4ኛዋ ባለግዙፍ ኢኮኖሚ ባለቤት እንድትሆን

አስችሏታል፡፡ ይህ እድገት የአውሮፓና የመካከለኛው ምስራቅ ባለሃብቶችን ኢንቨስትመንት እንደሳበ በገለፀው የኤሲያን ቢዝነስ ኮርፖሬት ዘጋቢ ፊልም ላይ አስተያየት የሰጡት የምጣኔ ሀብት ጠበብት ዶ/ር ክላርታ ጆርጅ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ the tiger economy ሲሉ Africa tiger economy ከሚለው የምርምር ፅሁፋቸው ላይ ጠቅሰው ገልጸውታል፡፡ በርካታ የውጭ ኢንቨስተሮች ወደዚህች የተስፋይቷ ምድር ስለመምጣታቸው ምክንያታችን ነው ሲሉ የሚገልፁት የተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ፣ የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት፣ የሰው ሃይል፣ የ5 ዓመት የግብር እፎይታ፣ ዘርፉ የሚፈልገውን መሰረተ ልማት ዝቅ ባላ ዋጋ አቅርባ መገኘቷን ዶ/ር ክላርታ Africa tiger economy ሲሉ በሰየሙት ፅኁፋቸው ላይ ገልፀውታል፡፡ ይህ ደግሞ የመለስ ራዕይ ውጤት ነው፡፡ እነዚህና ሌሎች መሰል አለም አቀፍ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ የተመለከቱ ሪፖርቶችን መነሻ በማድረግ ጥያቄ የሚቀርብላቸው የመንግስት የሥራ ኃላፊዎች ዕድገቱ ያለፉት 10 ዓመታት ነፀብራቅ እንደሆነ አፅንኦት በመስጠት ነው፡፡ ይህ አፅንኦታቸው ደግሞ ከየትም የመጣ ሳይሆን ይህን ሁሉ በኢንዱስትሪው መስክ የተመቻቸ እድል እየተጠቀሙበት የሚገኙት የውጭ ባለሃብቶች በመሆናቸው እና የአገር ውስጥ ባለሃብቶቻችን እና የመለስን ራዕይ ለማስቀጠል ቃል የገቡቱ ከራዕያቸው በተቃራኒው መጓዝን አለማቆማቸው በፈጠረው ስጋት መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ የመለስን ራዕይ እናስቀጥላለን ሲሉ የተመለከትናቸው ባለሃብቶች በብዛት ባሉበት ሀገር ላይ በቅርቡ እንኳን ቦሌ ለሚ በተባለው የኢንዱስትሪ ዞን ሲረባረቡ የነበሩት 20 የሚደርሱ ኩባንያዎች የውጭ መሆናቸው የሚያስተዛዝብና ቃል አባይነታቸውን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

የመለስ ራዕይ በከፊልም ቢሆን እየቀጠለ የሚገኘው በታላቁ የህዳሴ ግድባችን እና በአረንጓዴ ልማት ላይ ብቻ ይመስላል፡፡ ለዚህ ደግሞ የታላቁን መሪ ሁለተኛ የሙት አመት ምክንያት በማድረግ ሁሉም በችግኝ ተከላ ላይ ተሰማርቶ መታየቱ በቂ ማሳያ ነው፡፡ ታዲያም በችግኝ ተከላ ላይ ተጠምደው ያየናቸው የተለያዩ የመንግስትና የግል ተቋማት ሰራተኞች ከጋዜጠኞች ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ዛሬም የመለስን ራዕይ እንደሚያስቀጥሉ ነው ሲናገሩ የሰማነው፡፡ አንዳች እንኳን አስቀጠልን የሚል ዜና መስማትና ማየት አልተቻለም፡፡ በእርግጥ አስቀጥለው ቢሆን ኖሮ ማስቀጠላቸውን የሚናገርላቸው ተገልጋዩ ህብረተሰብ ነበርና አንድም መስካሪ ተገልጋይ በየትኛውም ዘርፍ

ላይ አለማየታችን የመለስ ራዕይን የማስቀጠል ቃል ኪዳናችን እየታጠፈ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

እገሌ የተባለ መስሪያ ቤት ሰራተኞች የመለስን 2ኛ ሙት አመት በዘከሩበት በዓል ላይ የመለስን ራዕይ እንደሚያስቀጥሉ ቃል ገቡ የሚል ዜና ሰሞንኛ የሚዲያዎቻችን የዜና ፕሮግራም ማሟሻ ነው፤ ጥሩ፣ ግን ቃል ከገቡ እኮ ሁለት ዓመት ሞላው ነው የእኛ ጥያቄ፡፡ ታዲያ በእነዚህ ሁለት ዓመታት በመንግስት በኩል የታላቁ መሪ ራዕይ የሚሳካባቸው የተለያዩ መደላድሎችም ሆኑ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች በስፋት ቢሰጡም ወደታች በወረድን ቁጥር በመንግስት (በቀበሌ በሉት በወረዳ፣ በክፍለ ከተማ እና ዞን) መዋቅሮች አሁንም ተገልጋዩን መበደል፣ ማሰቃየትና መንጠቅ እየባሰበት ነው ያለው፡፡ የእገሌ ቢሮ ብለው የጠየቁት አንድ ሰራተኛ አንኳን ይኸው ብሎ ለማሳየት ሲያቃትት ማየት የተለመደ ነው፡፡ ለሁሉም ነገር ጉርሻ የሚናፈቅባቸው መዋቅሮች እየተበራከቱ ነው፡፡ የመለስ ራዕይን መሰረት ያደረጉ እና ራዕዩን ለማሳካት የሚያስችሉ የተለያዩ አዋጆችና ደንቦች እንዲሁም ህግጋት በበታች የሥራ ኃላፊዎች እየተጣሰና በምን አውቅልሀለሁ እየተናዱ ነው፤ ሌብነቱም ከላይ እስከታች በየመዋቅሩ  በሰንሰለት እየነጎደ ይገኛል፤ የዘንድሮውን ጨምሮ የተደረጉና በመደረግ ላይ የሚገኙ የመልካም አስተዳደር የንቅናቄ መድረኮች "የመለስን ራዕይ እናስቀጥላለን" ሲሉ በምናያቸው የሚዲያ አፈ ቀላጤዎች እየቀለጡ ነው፡፡

እሴት የተጨመረባቸውና ያለቀላቸውን ምርቶች በመላክ የሃገራችንን ህዳሴ ለማፋጠን በታለቁ መሪ የተቀመጠውና የተነደፈልን ራዕይን በቃላባይ ባለሃብቶቻችን መደፍጠጡ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እሴት ያልተጨመረባቸውን ምርቶችም ለማስገባትና ለማስወጣት በሚደረገው የጉዞ ሂደት ላይ የሚገኙ ትራንስፖርተሮች ዛሬ የታላቁን መሪ ራዕይ ቀርጥፈው በበሉ ላኪዎች፣ አስመጭዎች፣ የትራንስፖርት ባለስልጣን መ/ቤት አንዳንድ ባልደረቦች፣ የአንዳንድ የፍትህ ተቋማት  ኪራይ ሰብሳቢዎች እና የመንገድ ደህንነት ደንብ አስከባሪዎች፣ እጅ መንሻ በለመዱ የፀጥታ ሃይሎች  እያነቡ ነው፡፡ በርካታ የትራንስፖርት ባለንብረቶች እንደ ባለንብረት ሁሉ ሁሉ በጃቸውና  በደጃቸው እንደሆነ በሚቆጥሩ ቃላባይ መዝባሪዎች ሁሉ ከእጃቸው ሁሉ ከደጃቸው ወጥቶ አቤት የሚሉበት ጠፍቷቸው እያንጎላጁ ነው፡፡ ተቀጣሪ ረዳቶችና አሽከርካሪዎችም የመለስን ራዕይ ሊያስቀጥሉ ቃል በሰጡ አንዳንድ የከተማ ወሮበሎች (ደላሎች) እየተዘረፉ እና አቤት የሚሉበት የፍትህ መዋቅርም ፊቱን እያዞረባቸው የበይ ተመልካች ሆነዋል፡፡

በተንዛዛ የክፍያ ስርዓትና አፈፃፀም፣ ለህዝብ ትራንስፖርት የዱቤ አገልግሎት እንደሌለ እየታወቀ ለድንበር ተሻጋሪ ትራንስፖርት አገልግሎት በምዝበራ እና የራስን ለማግኘት በሚሰጥ እጅ መንሻ፣ በመንገድ ደህንነት አንዳንድ  ኪራይ ሰብሳቢ ደንብ አስከባሪዎች (ትራፊክ ፖሊሶች) በመለስ ራዕይ ላይ በሚደረግ ውስልትና እና በደላሎች “ግባ በለው“ ደባ ባለንብረት እንኳንስ የሚያተርፍበት፣ ለአሽከርካሪ ደመወዝና ለመኪናው ነዳጅ የጣር ያህል ሆኖበት በአንድ እጁ በማጨብጨብ ላይ ነው፡፡ ይህ ሁሉ የሚሆነው ደግሞ በመለስ ራዕይ እያነበነቡ በተግባር በሚያላግጡ በየደረጃው የሚገኙ ትከሻቸው የማይችለውን ኃላፊነት የተሸከሙ የሥራ ኃላፊዎችና ቅጥረኛ የበታች ሹሞቻቸው ነው፡፡

በኢንቨስትመንት ስም ከላይ የተመለከቱ ምቹና ህጋዊ ሁኔታዎችን አይተው ወደ ሃገራችን የሚገቡ የውጭ ኩባንያዎችም የትራንስፖርቱን እና የወጪ ንግድ ዘርፉን አንዳሻቸው ሲያመሳቅሉ ሃይ ባይ የላቸውም፡፡ ይልቁንም የመለስን ራዕይ ሊያሳኩና አንዳች አስተዋፅኦ በማበርከት ለሃገራችንም ሆነ ለራሳቸው የሚጣደፉ የትራንስፖርት ባለንብረቶች ላይ የሚያፈጠው አይን የበዛ መሆኑን እያየንና እያደመጥን ነው፡፡

ለሃገሪቱ የጀርባ አጥንት በሆነው የውጭ ምንዛሬ ግኝታችን ግንባር ቀደም ለሆነው የትራንስፖርት ዘርፍ ታላቁ መሪ ራዕያቸውን ይፋ ያደረጉ ቢሆንም፣ ራዕያቸውን በበሉና ቃልኪዳናቸውን ባጠፉ ግለሰቦች ዛሬ ላይ የሚወጣም ይሁን የሚገባ እቃ ጭኖ ጅቡቲ ላይ ሳያራግፍ፤ አልያም ወደተፈለገው ቦታ ሳይሄድ  ለበርካታ ቀናት መቆም የአንድ ቀን ያህል እየተቆጠረ ነው፡፡

የወጪ ንግዳችንን በማሳለጥና በማቀላጠፍ የኢትዮጵያን ህዳሴ እውን እናደርገው ዘንዳ የተለያዩ አዋጆችና ደንቦች ቢወጡም መሰረተ ልማቱም ምቹ እንዲሆን ቢደረግምና ቢበዛ በሁለት ቀን ተኩል  ፉት የሚሏት የጅቡቲ መንገድ በአጃቢነት ታፔላ የተሰማሩ ኪራይ ሰብሳቢ የፀጥታ ሃይሎችን የአበል ክፍያ ለማሳደግ ሲባል፤ ሁለት ጊዜ ደርሰው ለመመለስ በሚያስችል  ቀናት እንዲሄዱ ሲደረግም ለምን ብሎ የሚቆጣ የጠፋው የታላቁን መሪ ራዕይ እናስቀጥላለን በሚሉ የአፍ አራጋቢዎች ራዕያቸው እየተደፈጠጠ በመሆኑም እንደሆነ አፅንኦት ሰጥተን ያጤንነው የጠራራ ፀሃይ ክስተት ነው፡፡

በእርሳቸው ራዕይ ልክም ባይሆኑ፣ በመሰረተ ልማቱ ዘርፍ ያሉ እንቅስቃሴዎች ተስፋቸው የሚያኮራ ነው፡፡ በውሃ፣ መብራትና ቴሌኮሙኒኬሽን ሴክተር ያሉ ችግሮች ምንጭ

የመለስን ራዕይ በሚያስቀጥሉ የልማት ሀይሎች የተከሰቱ ሳይሆን ቃላባይ በሆኑ የበታች ቅጥረኛ ሰራተኞችና ስርዓቱን ለመመዝመዝ በተደራደሩ ግለሰቦች መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ፌደራላዊ ሥርዓቱን በሁለት እግሩ ለማቆም የሚደረገውን ጥረትና የታላቁ መሪ ራዕይም በጥሩ ሁኔታ ላይ ከሚገኙ ወሳኝ ጉዳዮቻችን መካከል የሚገኙ ቢሆንም በዚህም ላይ የሚወሰልቱ ጥቅመኛ ግለሰቦች እየበዙ እንጂ እየተመናመኑ አለመሄዳቸው በታላቁ መሪ ራዕይ ላይ የሸፈቱ አስፈፃሚ አካሎች በመኖራቸው መሆኑም ሊደብቁት የማይቻል ሃቅ ነው፡፡

በዴሞክራሲያዊና በሰብአዊ መብቶች ጉዳይ የመለስ ራዕይ እንኳንስ ለኢትዮጵያ ትሩፋቱ ለአፍሪካም የተረፈ ስለመሆኑ አለም መስክሯል፡፡ ያም ሆኖ ግን ሀሳብን በነፃ በመግለፅ መብትና በፕሬስ ነፃነት ስም በሃገሪቱ ላይ የሚወሰልቱ እና የሚደራደሩ መብዛታቸውና ስለመብዛታቸው ተጨንቀን ከሀገሪቱ ህግጋቱ ጎን አለመቆማችን፣ ቆመንም አለመጮኻችን በመለስ ራዕይ  ላይ የመወስለታችን ወይ ራእያቸው ፈፅሞ ያልገባን የመሆኑ ማሳያ ነው፡፡

መማርና ህክምና ማግኘት ለሁሉም ዜጎች እኩል የማይነጥፍ መብት መሆኑን በማመንና ታግለው በማታገል ራዕያቸው እውን ይሆን እንድ የዘረጉት ስርዓት በብዙ መልኩ የተሳካ ቢሆንም ቃል አባይ በሆኑ ኃላፊዎች ተመሳጣሪነት አንዳንድ የግል ትምህርት ቤቶችና የህክምና ተቋማት የታላቁን መሪ ራዕይ ወደፊት ሳይሆን ወደኋላ እንዲወስደን እየታተሩ መሆኑም ሊታወቅ ይገባል፡፡

ብዝሃነታችን በብዙ መልኩ በሚገለፅበት ሃገር ላይ በአንድ ቋንቋና በአንድ ሃይማኖት ተገድበን የነበርንበትን ዘመን እንሻገርና ያ ዘመንም እንዳይመለስ በታላቁ መሪ የተቀየሰልን ንድፍ በሃይማኖት አስባብ በሚንቀሳቀሱ ነዳፊዎች ሲኮሰምን ዝም ማለታችንም በታላቁ መሪ ራዕይ ላይ እያፌዝን መሆኑ ሊገባን ይገባል፡፡ ብቻ በጥቅሉ፣ እኒህ ጥቂቶቹ ናቸው እንጂ እናውራው ከተባለ በፀጉራችን ልክ ነው፡፡ ስለሆነም እራሳችንን በየደረጃችን፣ በየተሰጠን ኃላፊነት እና በየተሰማራንበት መስክ እንመርምር፡፡ ያለፈውም ይለፍ፤ ለታለቁ መሪ ሶስተኛ ሙት አመት ስንገናኝ ‹‹እናስቀጥላለን›› በሚል ዜና ሳይሆን ማስቀጠላችንን ከሚያረጋግጡልን ማሳያዎችና ዋቢዎች ጋር እንዲሆነ የበኩላችንን አበርክቶ ለዚህች ለሃገራችን አድርገን፣ በአናቱም ከአህጉረ አፍሪካ አራተኛ ሳይሆን አንደኛ ባለግዙፍ ኢኮኖሚ ሆነን እንዲሆን  ግድ ይለናል፡፡ የምርጫ ወሮች ልክ እንደመስቀል ወፍ በየ5 ዓመቱ ብቅ እያሉ በመለስ ራዕይ የተነደፈውን ዴሞክራያዊና ፍትሀዊ ምርጫ ለማካሄድ

የሚያስችሉ ህግጋቶችና ተቋሚት ላይ ቢያላግጡበትም ቅሉ በምርጫ 97 ወቅት የተበታተኑ ፓርቲዎችን በማሰባሰብ ዓለማ የተቋቋመው *ቀስተደመና* አመራር የነበሩት ፕ/ር መስፍን ወልደማርያም ለሽገር የጨዋታ ፕሮግራም እንዳሉት ፖለቲካ ቁርጠኝነትን፣ አምኖ መነሳትን እና ማወቅን የሚጠይቅ ሆኖ ሳለ፣ ስልጣን የአገልግሎት መሳሪያ መሆኑን ባላወቁ ሃይሎች መሞላቱ እና እንኳንስ ያኔ አሁም ዝግጁ የሆነ ፓርቲ እንደሌለ ተገንዝበን በየአስባቡ የእራሳቸውን ዝቅጠት በሥርዓቱ ላይና በመለስ ራዕይ ላይ ሊያላክኩ የሚሹ ሃይሎችን ዝም ማለት ከሁሉ በላይ የሉዓላዊነታችን መገለጫ በሆነው ህገመንግስታዊ ስርዓት ላይ እያላገጥን መሆኑን በቅጡ  መረዳት የሚገባን ሰዓት ላይ መሆናችንን ልናሰምርበት ይገባል፡፡